# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)

ሐምሌ 8 ቀን 2008 ዓ ም

<u>ኢሕአፓ ለጎንደር ሕዝብ ትግል ሙሉ ድጋፉን ያረጋግጣል</u>

በኢሕአፓ የትግል ታሪክ ውስጥ ጎንደርና የጎንደር ሕዝብ ያላቸው ቦታ ከፍተኛ ነው። የጎንደር ሕዝብ ኢሕአፓንም ሌሎች ሀገር ወዳድ ድርጅቶችንም ደግፎ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሏል። አራጁ መላኩ ተፈራና አረመኔው ደርግ፤ እንዲሁም ዘረኛውና ጸረ አማራው ወያኔ ይህን ታጋይና ሀገር ወዳድ ሕዝብ በተለየ ደረጃ አጥቅተውታል። የጎንደር የሰማዕት ታሪክ የኢሕአፓ ታሪክ ማዕከል ሆኖም ቆይቷል ።

ኢሕአፓ በጎንደር እየተካሄደ ያለውን ጸረ ወያኔ ትግል ሙሉ በሙሉ ይደግፋል። ወያኔም ማጥቃቱ፤ ንብረታቸውን በእሳት ማጋየቱ፤ መሬትና ማንነትን ለማስከበር ቆርጦ መነሳቱን ያደንቃል። የሕዝብን ቁጣ ሊያበርዱና ሊያሰናክሉ፤ ሰላም በሚል ቀረርቶ ትግልን ሊያኮላሹ፤ በፖለቲካና ኢትዮጵያዊነት ዙሪያ ማበር መደራጀት ሲገባ የጎጥ ሰልፍና ልማት ተብዬውን ሊሰብኩ የተነሱትን ሁሉ ኢሕአፓ ያወግዛል። ወቅቱ የመራራና የቆራጥ ትግል ወቅት ነው። ወያኔ ሕዝብን በጅምላ በመፍጀት ትግሉን ለማፈን መጣሩ የሚጠበቅ ነው። በግድ ወደ ትግራይ የተጠቃለለው መሬትና ማንነቱ የተካደውም ሕዝብ ቆርጦ መነሳቱ የሚመሰገን ነው። የአፍራሽና የቅጥረኞች የአዞ እንባን ረግጦ ትግልን መቀጠል አስፈላጊ መሆኑን ትግልን ለሚያውቀው የጎንደር ሕዝብ ሊያስተምር የሚቃጣ ሊኖርም አይችልም። ከጎንደር ሕዝብ ጎን  በተጨባጭ መቆም ጊዜው አሁን ነው። ሀገርን ማስመለስና ድንበርን ማስከበር፤ ማንነትን ማስረገጥ ለነገ የሚባል ትግል አይደለም። በመሆኑም ኢሕአፓ በአካባቢው ያሉትን አባላትና ደጋፊዎች የትግሉ አካል ሆነው እንዲሰለፉ ጠርቷል። በሰበብ አስባቡም ከወያኔ ጎን ቆመው የነበሩትም በጊዜ ከሕዝብ ጎራ እንዲቀላቀሉም ጥሪ ያደርግላቸዋል። ይህ ጸረ ወያኔ ትግል መጠቃት የለበትምና ሀገር ወዳድ ኃይላት ሁሉ - በያሉበት -- ሊታደጉት፣ ሊረዱት፣ ሊያጠናክሩት መነሳት አለባቸውም ይላል። ከዚህ ተያይዞ መነሳት ያለበት ዋናው ጉዳይ ግን የጎንደር ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ጥቃት በተመለከተ ባእዳን ዝምታን መምረጣቸውን ነው። ጸረ አማራው የወያኔ ፖለቲካ ከእነዚህ ክፍሎች ከድሮ ጀምሮ ሲደገፍ የቆየ ነውና የሕዝቡን ትግል ማስተጋባትም ሆነ ለድል ማብቃት የኢትዮጵያውያን ግዳጅ ሆኖ ይገኛል። የጎንደር ሕዝብ አመጽ፣ ወያኔ ሊል እንደሞከረው፣ የባዕድ ታጣቂ ኃይሎች እርምጃ ሳይሆን፤ የማንም ድርጅት ድርጊት ሳይሆን የሰፊው ሕዝብ የእምቢታ ውጤትና አመጽ መሆኑም መታወቅ ያለበት ነው ።

ኢሕአፓ ከጎንደር ሕዝብ ጎን ተሰልፏል !!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

**EPRP**
**P.O.BOX  73337**
**Washington DC,  20056**
**USA**

**Email  ESPIC@aol.com**
**Website  www.eprp.com**

**EPRP**
**BP  30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel.  202 291 4217    Fax:  202 291 7645**